ቁርኣን የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አርባ ዓመታቸው ላይ ሳሉ ወረደ

ኢብኑ ዐባስ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንዲህ ብለዋል፦ ቁርኣን የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው
ላይ ይስፈን አርባ ዓመታቸው ላይ ሳሉ ወረደ። በመካ አስራ ሦስት ዓመታት ቆዩ። ከዚያም በስደት ታዘዙ። ወደ መዲና ተሰደውም አስር ዓመታትን ቆዩ። ከዚያም ነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አረፉ። [ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ኢብኑ ዐባስ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- ወሕይ (መለኮታዊ ራዕይ) በአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ላይ የወረደውና የተላኩበት ዕድሜ አርባ መሆኑን፤ ከወሕይ መውረድ በኋላም በመካ አስራ ሶስት አመት መቆየታቸውን፤ ከዚያም ወደ መዲና እንዲሰደዱ እንደታዘዙና በመዲናም አስር አመታት እንደቆዩ፤ ከዚያም ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በስልሳ ሶስት አመታቸው እንዳረፉ ተናገሩ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/65050